# የአሥተሳሰብ ለውጥ(Mindset) ለወሳኝ ትግል!

**ከኦርቶዶክስ፣ከኢትዮጵያና ከሠንደቋ ጭምር እንዲጠፉ የተፈረደባቸው አማራውና ኢትዮጵያዊው ውገን፣ የቀረበላቸው ብቸኛ አማራጭ፣ዓላማና ግብ ያነገበ ድርጅት ፈጥሮና ታጥቆ ተገዳዳሪ ሆኖ መውጣት ነው፡፡**

## የነፃ አውጭዎች ዓላማና ግብ!

-የትግሬ ትህነግ እና የኦሮሞ ኦነግ! በ1983ዓም ግንቦት-ሰኔ ወር አዲስ አበባ እንደገቡ፣አማራን አግልለው፣ ከተለያዩት ብሔር ብሔረሰብ ሠዎችን በመመልመል፣የኢትዮጵያን አንድነት ለማጥፋትና የወደፊት የመገንጠል ዓላማና ግባቸውን ለማመቻቸት  ሲሉ፣በዘር በተከፋፈሉ በዘጠኝ(9)መንግሥታትና ባንዲራዎች የመሸንሸን ኮንፈረንስ አካሂደው፣የሽግግር መንግሥት አቋቁሙ፡፡

-አማራውን ለመጉዳት ሲሉ አማራው በብዛት የሚኖርባቸውን መሬቶች ቆራርሰው የዝሆኑን ድርሻ ወደራሳቸው  ከጠቀለሉ በኋላ ለሌሎችም አከፋፈሉ፡፡ለወደፊት ሊጠቀልሏቸው ላሰቧቸው አንዳንድ ብሄረሰቦችም ሰፊ መሬት ከለሉላቸው፡፡

-ቀጥሎም ዘርና ቋንቋን መሠረት ያደረገ አማራን፣ኦርቶዶክስንና ኢትዮጵያዊ ወገንን ከኢትዮጵያና ከሠንደቋ ጭምር ገዝግዞ የሚያጠፋ ህገ መንግሥት አፀደቁ፡፡

**ልብ እንበል! በዚህ ወቅት ነው፣ ኢትዮጵያም በገንጣዮች እጅ ወድቃ በዘር ሥትሸነሸን፣እንደአገር ቀጣይነቷ ጥያቄ ውስጥ መግባት የጀመረው፡፡ አማራ፣ ኦርቶዶክስና ኢትዮጵያዊ ወገንም ከኢትዮጵያ ጭምር  እንዲጠፉ የተፈረደባቸው፡፡በወቅቱ ከእነፕሮፌሰር አሥራት ጎን ብንሠለፍ ኖሮ፣ዛሬ አሸናፊዎች እንሆን ነበር፡፡**

-ሁለቱም የትግሬና የኦሮሞ ነፃ አውጭዎች! ነፃ የሚወጡት ከአማራውና ከኢትዮጵያዊ ወገን እንደሆነ፣ ፕሮግራም ፅፈው፣ኢትዮጵያን ቢገዙም ባይገዙም፣ይህንን  ዓላማቸውን ሲያጠናቅቁ ምንጊዜም የመጨረሻ ግባቸው ነፃ መውጣት (መገንጠል) ነው፡፡

-ሁሉም የትግሬ ድርጅቶች የትህነግ አሥተሳሰብ ተሸካሚዎች  የመሆናቸውን ያህል፣የኦሮሞ ድርጅቶችም ከአቢይ መንግሥት ጭምር የኦነግ አሥተሳሰብ ተሸካሚዎች ናቸው፡፡

-የኦሮሞ ድርጅቶች ከእንግሊዝ ሥብሰባ በኋላ፣ አሜሪካ አገር ሁሉም  ከእነመራራ ጭምር በተገኙበት ተሠብስበው፣በኢትዮጵያ ውሥጥ "የኦሮሚያ ሪፓብሊክ አገር" ፈጥረዋል፡፡ ዛሬ ከላይ እሥከታች ቢሮክራሲውን በራሳቸው ሠዎች ሞልተው የሚለማመዱትም ለዚህ ነው፡፡ያልነቃህ ንቃ!!!

-እሥከገዙን ድረስ የቆሙለትን አጥፊያችን የሆነውን ዓላማና ግብ ለማሳካት፣ "ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቅ"የመሳሰሉ የሕዝብን ልብ የሚያማልሉና የተለያዩ ታክቲኮች በመጠቀም፣በመንገዳቸው ላይ የቆመውንም በመግደል እየፈፀሙት ነው፡፡

-ትህነግ ሥልጣን ሲያጣ  ትግል ሲጀምር ያቀደውን የመገንጠል ግብ ለመተግበር  ጦር ሠብቆ እንደተነሳው ሁሉ፣ሌሎቻችን ተጠናክረን ከቆምንና እነአቢይም አቅም አንሷቸው እንደትህነግ ከሥልጣን ከተገለሉ፣ "የመገንጠልን የግብ ካርድ" ይመዛሉ፡፡

እነአቢይ እስካሁን ያልተገነጠሉት ማሳካት የሚገባቸውን ሁሉ ባለማጠናቀቃቸው እና ሌላውን እያደሙ የሚያገኙትን ጥቅም ላለማጣት ብቻ ነው፡፡ ጉልበታቸው ከበረታ ኢትዮጵያን በኦሮሚያ ሥም ይቀይራሉ ፣ ሠንደቃችንንም በኦነግ ባንዲራ ይተካሉ፡ ኦነግንም በሸኔ አሰማርተው የሚገድሉን ለግባቸው ነው፡፡

## የአማራውና የኢትዮጵያዊው ወገን ከኦርቶዶክሱ ጭምር  ዓላማና ግብ አለው?

**የትግሬና የኦሮሞ ነፃ አውጭ ድርጅቶች! ዓላማና ግብ ቀርፀው መታገል ከጀመሩበት ጊዜ አንሥቶ እሥከዛሬ ድረስ፣ ነፃ የሚወጡት ከነበረው ሥርዓት ብቻ ሳይሆን፣ ከአማራው፣ከኦርቶዶክሱ፣ከኢትዮጵያዊ ወገን፣ ከኢትዮጵያና ከሠንደቋ ጭምር እንደሆነ፣**ከጥቂቶች በሥተቀር፣ብዙሀኑ አማራና ኢትዮጵያዊው ወገን ከኦርቶዶክሱ ጭምር ወይ አልተገለፀለትም ወይም ገብቶት መፍትሄ አጥቷል፡፡

**ቢገለፅለት ኖሮ፣**

(1)ኢትዮጵያም በብሄር ብሔረሰቦች ተገፍትራና ተቦርቡራ ቀፎዋ እንደቀረና የአሜሪካን አጥኚዎች

 በ2030 ዓም ከዓለም ካርታ እንደምትጠፋ የደገሱልን መሆኑን ተረድቶ በአንድነት ይነሳ ነበር፡፡

(2)የኢትዮጵያን መጥፋት ለማሳለጥ በኢትዮጵያ ሥም የሚጠራው በአቢይ የሚመራው የኦሮሞ መንግሥት የኦሮሞህገመንግሥት፣የኦሮሞ ፌደራል፣የኦሮሞ መከላከያ፣የኦሮሞፍትህናሥርዓት፣እንደሆነና እንደሚያጠፋው ቢያውቅ ኖሮ፣ ድርጅት ፈጥሮ ጦሩን ሠብቆ፣ለማሥወገድ በቁርጠኝነት ይነሳ ነበር፡፡

(3)"መንግሥትይድረሥልኝ፣የህግየበላይነትይከበር፣መከላከያውለምንአይዋጋም፣ፌደራልና ፍትህ"የሚባሉትን ከሚገድለው መንግስትና ህግ ተብዬው አይጠብቅም ነበር፡፡ዕምነትም አይኖረውም  ነበር፡፡

(4)በአማራነት ተደራጅቶ ራሱን ሳያድን፣ ኢትዮጵያን ሊያድን እንደማይችል ይረዳው ነበር፣

(5)አማራውና ኢትዮጵያዊው ወገን  የጀመረውን ትግል ቀጥሎ፣ሥርዓቱን ከሥር ከመሠረቱ ሳይነቅል፣አቢይ ኢትዮጵያን ሥለጠራና እሥረኛ ሥለፈታ፣ትጥቅ ፈትቶ ዕልልታውን አያቀልጥም፣ድጋፍም አይቸርም ነበር፡ ከኢሕአዴግ ወደብልፅግና  ሥሙን የቀየረው የኦሮሞ ቡድንም፣ የኦሮሞን የበላይነት ሥልጣን እንዳያጠናክር፣የዛሬው መሳደድና መገደል እንዳይመጣም ቀድሞ ይታገል ነበር፡፡

(6)አገርን በብሔር ገነጣጥሎና የኢትዮጵያን አንድነት አጥፍቶ፣"መከላከያው ብሔር የለውም፣በኢትዮጵያ አንድነት የቆመ ነው፣ፓርላማ ሥንገባ እንደብሔር ሳይሆን እንደኢትዮጵያ ነን" እያለ አቢይ!ዓላማውን ለማሳካት የተለያዩ ታክቲኮችን ከውሸት ጭምር፣ እየተጠቀመ  ሲቀልድብን "በቃኝ" ብሎ ራሱ ይደራጅ ነበር፡

(7)የራሱ ፖለቲካና መሣሪያ የታጠቀ ድርጅታዊ ወኪልና አመራር ይኖረው ነበር።

አጥፊዎቹ  ለዓላማቸው የሚጠቀሙባቸውን ታክቲኮች የመረዳት አቅም ካላጣ በሥተቀር "እነ አቢይ፣ ይዋሻሉ፣መከላከያው አይዋጋም፣ የአማራ ክልል ነፃ ሳይወጣ እንደወጣ ተነገረ፣አማራዎች በወለጋ አለቁ፣ አዳነች አበቤ በኦርቶዶክስ፣ወዘተ" ተብሎ ዜናው ሲለቀቅ፣ቁርጦለት ይነሳ ነበር፡፡

አጥፊዎቻችን በ30ዓመት ውስጥ በድርጅትም በትጥቅም ሲገዝፉ፣የእኛ አካሄድ ትግል ሥንጀምር ወደነበርንበት እየመለሰ፣እየመላለሰ ሥለሚወስደን፣እስከዛሬ ድረስ ከተናጠል፣ከተበታተነ፣ ከተሳከረ እና ግራ ከተጋባ የትግል አዙሪት ውስጥ እንድንወድቅ አድርጎን አይኖርም ነበር፡፡

ይህ  አካሄዳችን እኛንም ኢትዮጵያንም እንደሚያጠፋ  ቢገባን ኖሮ፣**እኛ መሣሪያ እንዳንይዝ እየተቀማን፣ ኦሮሞ እስከአፍንጫው አይታጠቅም ነበር።መከላከያውንም ኦሮሞው  በብቸኝነት አይዘውም ነበር**።

አቢይ መከላከያው እንዳይዋጋ ካደረገ በኋላ፣አማራውን አሥወረረ፡፡ ለራሱ ሥልጣን አሥጊ ሲሆንበት፣ የአማራው አዳኝ መስሎ፣የኦሮሞን መከላከያ በኢትዮጵያ ሥም  እየጠራ፣ዘመትኩ ካለ በኋላም

አማራው የራሱን ራያን ነፃ እንዳያወጣ "ከቆቦ በኋላ አታልፍም" ብሎ ሲያስቆመው፣ጠላትነቱን ተረድቶ ገፈታትሮ  ይገባ ነበር፡፡በወልቃይትም ጥያቄ አማራው እንጅ፣የኦሮሞው መንግሥትም ሆነ ብአዴን እንደማያገባቸው መረዳት ይችል ነበር፡፡በአጠቃላይ  እነኚህ ሁሉ የሚሠሩብን ወንጀሎች **እንዲከበሩ** ሳይሆን **እንዲቀበሩ** ነበር መታገል የነበረብን፡፡ዛሬም ከነቃን ቢዘገይም አልመሸምና ወደ**መፍትሄው** እንሂድ፡፡

## መፍትሄ ለዓላማና ግብ!

የአማራው ሕዝብ ከትግሬው በተጨማሪ ፣በአቢይ የኦሮሞ መንግሥት ጭምር ተከብቦ ከሚጨፈጨፍበት ከጨርሶ መጥፋት ሊድንና በአሸናፊነት ሊወጣ የሚችለው፣"አንድነን፣ኢትዮጵያን ሊያፈርሷት ነው፣ወዘተ" እያለ ከ30ዓመት በላይ ተጉዞበት በጠፋበት መንገድ ሳይሆን ፣መሬት ላይ ያለውን ዕውነታ ተረድቶና ነቅቶ፣ ለሥር ነቀል ለውጥ በአንድነት ሊያሠልፉት በሚችሉት ጉዳዮች ላይ ብቻ ማተኮር ሲችል ነው፡፡ይኸውም

(1)ከሁሉ በፊት **የአሥተሳሰብ ለውጥ (Mind set)** ማድረግ ሲችል ነው፡፡

ቀጥሎም "አጥፊዎቻችን ትህነግና ኦነግ ቆርሰው የጣሉንንና ያጠሩትን ክልል አንቀበልም፣ **አማራ ብሔር አለው፡፡አገሩና ክልሉ ግን ኢትዮጵያ** ናት፡፡ኦሮሞ ከመምጣቱ ከ940ዓም በፊት ጀምሮ በነበርንበት በአገራችን በየትኛውም ቦታ የመኖርና የመሥራት መብት አለን"በማለት ከመሳሪያ በፊት ልባችን ይታጠቅ፡፡

(2)ልባችን ከታጠቀ፣ እንደ እሥከዛሬው ያዝ ለቀቅ ሳይሆን፣የፖለቲካ ዕውቀትና ንቃት ባላቸው ሠዎች የሚመራ፣"ዓላማና ግብ" ያነገበ፣ጠንካራና ጥራት ያለው፣ከማንም ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ **ሁለገብ** ማለትም በቅድሚያ **በህቡዕ፣ጉልበት ሲፈረጥም በገሀድ** የሚታገል **የአማራ ሕዝባዊ አንድነት ድርጅት** ማቋቋም ነው፡፡

ይህንን ማድረግ ከተቻለ፣ፋኖውን፣ልዩ ኃይሉንና ሚሊሻውን በአንድ አሠባስቦና በፖለቲካ ንቃት አንፆ፣ በውስጣቸው የተጠቀጠቁትን የትግሬ፣የኦሮሞና የባንዳ አማራዎችን ሠርጎገቦች በመመንጠር፣የአማራ ጦር አቋቁሞ የማይነቃነቅ አቋምን ማሳወቅ ነው፡፡በዓለማችን የህቡዕ ትግል በ5-7ሠዎች ተጀምሮ ያውቃል፡፡

(3) የአማራው ሕዝብ መሠረታዊ ጠላቶች በትህነግና በኦነግ አማራን ለማጥፊያ የመሠረቷቸውና ያፀደቋቸው **ሦሥቱ " ህገመንግሥቱና የዘር ፌደራሊዝሙ ከሥርዓቱ ጭምር"** መሆናቸውን አምነን፣እንደአንድ ሠው ተነሥተን ፣በመሠባሰብ፣እንደእሰከዛሬው ያዝ ለቀቅ ሳይሆን በፅናት ታግለን ለማሥወገድ መቁረጥ የመጀመሪያው የትግል"ሀ ሁ " መሆኑን መቀበል ናቸው።

እነኚህን ሦሥቱን የአማራ ጠላቶች ለመጣል የሚገለገሉባቸውን ድርጅቶች በዋናነት ብልፅግናንና በውሰጡ ያቀፋቸውን እነብአዴንን እነኦህዴድን የቤኒሻንጉልን ወዘተ በአንድ ቅርጫት ውሰጥ አሥቀምጦ መታገል ነው፡፡

በአጠቃላይ ሥርዓቱ፣መንግሥቱም፣ህገ መንግሥቱም፣ፌዴራሉም ሆነ መከላከያው ቀደም ሲል የትግሬዎች፣ ዛሬ ደግሞ የኦሮሞዎች ጥቅም ማሥጠበቂያና እንዲሁም የአማራን ሕዝብ ለዕርድ እንዲያቀርብላቸው በጥቅምና በተላላኪነት የያዙት የብአዴን እንጅ የአማራው ሥላልሆነ እምቢተኝነትን እያዳበርን የራሳችንን ህልውና ለማሥከበር፣እኛ አማራዎች የቱትሲዎችን፣ ኢትዮጵያዊ ወገን ደግሞ የአብርሀም ሊንኮልን መንገድ በመከተል፣የተነጠቅነውን መብትና አገር በእጃችን ማድረግ ከመቻልም አልፈን የመገንጠል ምኞታቸውንም ፈጥነን ከተደራጀን ማክሸፍ እንችላለን፡፡

እነኚህ በእያንዳንዱ አማራ ደም ሥር ውሰጥ ከገቡ እና ከነቃን ወገናችንን ለድል እናበቃዋለን።

በዚህ ሥርዓት ውስጥ፣ **የኢትዮጵያዊ ወገኖች ብሔር እና ክልል ባይኖራቸውም፣አገራቸው "ኢትዮጵያ"** እንደሆነች ቃሉ ሥለሚናገር፣ ቀበቷቸውን አጥብቀው ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን አሥተባብረው የአንድነት ወይም የህብረት ድርጅት ፈጥረው፣እንደአማራው በሁለገብ ትግል የራሳቸውን ጦር ገንብተው ይታገሉ፡፡ የአማራውም ሆነ የኢትዮጵያዊው ወገን የድርጅቶቻቸው ዓላማ የተለያዩ ቢሆኑም፣ የመጨረሻ ግባቸው ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ማድረግ መቻል ሥለሆነ ትግላቸውን እየተደጋገፉ ፍፃሜ ማድረስ ነው፡፡ በራሳችን ላይ ከተማመንና በዚህ መንገድ መታገል ካዘወተርን ዛሬ ተራራ መሥሎ የሚታዩን ነገ ሜዳ ሆኖ፣ድል

መቀዳጀት እንደሚቻል ታሪክ አሳይቶናል። ከዚህ ውጭ "አንድ እንሁን" ብንል ከ30ዓመቱ አካሄዳችን የተለዩ አይሆንም፡፡“ዓላማህን በማሳለጥ ግብ ለመድረስ፣ጠላትህን አጥብቀህ ጥላ!”